## ሆሣዕና

ሆሣዕና በአርያም
ሃሌ ሃሌ ሉያ ፤ ሃሌ ሃሌ ሉያ።
መድኃኒት መጣልን ለሁላችንም
ሃሌ ሃሌ ሉያ ፤ ሃሌ ሃሌ ሉያ።
ምስጋና ይድረሰው ለአምላክ በመላው ዓለም።
ሆሣዕና /2/ በአርያም።

ሆሣዕና በአርያም
ሃሌ ሃሌ ሉያ ፤ ሃሌ ሃሌ ሉያ።
ብሩክ ነው የመጣው በኃያሉ ስም
ሃሌ ሃሌ ሉያ ፤ ሃሌ ሃሌ ሉያ።
እናከብረዋለን ከልባችን ለዘለዓለም
ሆሣዕና (2) በአርያም።

## ሆሣዕና በአርያም

ሆሣዕና (2) በአርያም ሆሣዕና በአርያም
ቅድስት ሀገር ሆይ ኢየሩሳሌም
ምስጋናሽ ብዙ ነው በመላው ዓለም
በአህያ ላይ ሆኖ ወደ አንቺ የገባው
ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት ነው፤

ሆሣዕና (2) በአርያም.......................
ኃይልና ሥልጣንም ባንድ ላይ ስላለው
ጠላቶች አፈሩ ሕዝብሽም ደስ አለው።

ሆሣዕና (2) በአርያም.......................
ሰውማ ቢዘምር ምን ያስገርመናል
ሆሣዕና ሰው ቀርቶ ድንጋይ ያናግራል።

ሆሣዕና (2) በአርያም ሆሣዕና በአርያም
ቅድስት ሀገር ሆይ ኢየሩሳሌም
ምስጋናሽ ብዙ ነው በመላው ዓለም

## ሰላምሽ ዛሬ ነው

ሰላምሽ ዛሬ ነው ኢየሩሳሌም
ወዳንች መጥቷልና አምላክ ዘላለም (2)
ሆሣዕና በአርያም እያሉ ዘመሩ
ሕጻናት በኢየሩሳሌም፤
አንቺ ቤተልሔም የዳዊት ከተማ
የሕዝቦችሽ ብርሃን መጣልሽ በግርማ (2)
ሆሣዕና በአርያም እያሉ ዘመሩ
ሕጻናት በኢየሩሳሌም፤
ሆሣዕና እያሉ አመሰገኑት
በኢየሩሳሌም አእሩግ ሕጻናት (2)
ሆሣዕና በአርያም እያሉ ዘመሩ
ሕጻናት በኢየሩሳሌም፤
ኪሩቤል መንበሩን የሚሸከሙት
መስቀል ተሸክሞ ሆነን መድኃኒት (2)
ሆሣዕና በአርያም እያሉ ዘመሩ
ሕጻናት በኢየሩሳሌም፤
የኢየሱስን ሕማም ደናግል አይተው
እያለቀሱለት ሄዱ ተከትለው
ሆሣዕና በአርያም እያሉ ዘመሩ
ሕጻናት በኢየሩሳሌም፤

## ሆሣዕና ለወልደ ዳዊት

ሆሣዕና (3) ለወልደ ዳዊት
አባቶች እናቶች ሕጻናት በሙሉ
ለዓለም መድኃኒት ሆሣዕና በሉ (2)

ሆሣዕና (3) ለወልደ ዳዊት
ባህያዋ ጀርባ አምላክ ቁጭ አለና
አሣየ ለሕዝቡ ታላቅ ትህትና (2)

ሆሣዕና (3) ለወልደ ዳዊት
ቤተ መቅደስ ገብቶ የሰላሙ ዳኛ
ይውጣ ብሎ አዘዘ ሌባና ቀማኛ

ሆሣዕና (3) ለወልደ ዳዊት

## ሆሣዕና እምርት

ሆሣዕና እምርት እንተ አቡነ ዳዊት (2)
ቡርክት እንተ ትመጽእ መንግስት (2)

ትርጉም፣
የታወቀችይቱ የድኅነት ቀን የምትመጣይቱ
ያባታችን የዳዊት መንግስት ቡርክት ናት።

## እም አፈ ደቂቅ

እም አፈ ደቂቅ ወሕጻናት አስተዳሎከ ስብሐተ (2)
በእንተ ጸላዒ (4) ከመ ትንሥኦ ለጸላዒ ወለገፋዒ(2)

ትርጉም፣
ከሕጻናት አንደበት ምስጋናን አዘጋጀህ
የጠላት ዲያብሎስን ምክሩን ታፈርስበት ዘንድ።